# ክሎዝላይን ክሉስ ቱ ጆብስ ፒፐል ዱ (Clothesline Clues to Jobs People Do)




## የአር አይ ኤፍ (RIF) መምሪያ ለቤተሰቦች

ይዘቶች (Themes)፧ ሙያዎች (Careers)፧ አልባሳት (Clothing)፧ የማህበረሰብ ረዳቶች (Community helpers)

የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፧ በዚህ የግጥም መጽሐፍ ውስጥ ለአንድ የተወሰነ ሥራ የሚውሉ ልብሶች በልብስ ማስጫ ገመድ ላይ ተሰቅለዋል። እና ለሥራው ፍንጭ ለመስጠት እንቆቅልሽ ቀርቧል። እነዚህን ልብሶች ማን እንደሚለብስ መገመት ይችላሉ? ከእነዚህ ሥራዎች ውስጥ አንዱ ለእርስዎ የሚስማማ ነው?

ደራሲ፧
ካትሪን ሄሊንግ እና ዲቦራ ሄምብሩክ (Kathryn Heling and Deborah Hembrook)

ሰዓሊ፧
አንዲ ሮበርት ዴቪስ (Andy Robert Davies)

## የማንበብ ጊዜ!



ከንባብ በፊት፧ የታሪኩን ርዕስ ያንብቡ እና ሽፋኑን ይመልከቱ። በሽፋኑ ላይ ለአንድ ልዩ ሥራ ማንኛውንም ፍንጭ ካዩ ይጠይቁ። ለተወሰኑ ስራዎች እንደ "ዩኒፎርም" ወይም "አለባበስ" ያሉ ቃላትን ግምት ውስጥ ማስገባት ይችላሉ።

በንባብ ጊዜ፧ በሚያነቡበት ወቅት "ከእነዚህ ልብሶች ጋር ምን አይነት ስራ አብሮ ይሄዳል? አንድ ሰው እነዚህን ልብሶች (ወይም ዩኒፎርም) ለብሶ ይህን ሥራ ሲሠራ የት አይተኸዋል? ምን እንዲህ እንድታስብ አደረገህ?" በማለት ይጠይቁ።

ከንባብ በኋላ ይጠይቁ፧

- በመጽሐፉ ውስጥ ምን ሥራዎችን አይተናል?
- በመጽሐፉ ውስጥ ምን አይነት ልዩ ልብሶች ወይም መሳሪያዎች ነበሩ?
- በመጽሐፉ ውስጥ ካሉት ሥራዎች አንዱን መሥራት ትፈልጋለህ? ለምን ትፈልጋለህ ወይም ለምን አትፈልግም?
- በመጽሃፉ ውስጥ ያሉት ሰዎች እንዴት ነው ረዳቶች የሚሆኑት?

## ሆን ተብሎ የሚደረግ ንግግር (INTENTIONAL TALK)

ጽሁፎችን እንደገና ማንበብ ለጀማሪ አንባቢዎች ጠቃሚ ልምድ ነው። መጽሐፍን እንደገና ማንበብ ልጆች በታሪኮች ውስጥ ካሉ ገፀ-ባህሪያት ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያዳብሩ እና ዝርዝሮችን በራሳቸው ተሞክሮ ውስጥ ካሉ አፍታዎች (ለምሳሌ በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱትን ልብሶች ወይም ስራዎች እውቅና በመስጠት እና በእውነተኛ ህይወት ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ መለየት)። በተጨማሪም የልጆችን ዓይኖች ለአዳዲስ እና የተለያዩ ሰዎች እና ልምዶች ሊከፍት ይችላል (ለምሳሌ, ለልጅዎ የማይታወቅ ስራ ወይም ልብስ ካለ, ያንን ሚና ለመግለጽ እድል ይሰጣል። እንዲሁም፤ በታሪኩ ውስጥ በሙሉ ለፖስታ አጓጓዥ ልዩ ትኩረት መስጠት ይችላሉ። ምን እየሰራች ነው? በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ምን ይሆናል? በመጨረሻም ሰዎች በመጽሐፉ ውስጥ እየሰሩ ያሉትን ሁሉንም ነገሮች ለማገናኘት ይሞክሩ።

## ተዛማጅ ተግባራት

**የስራዬ ዘፈን ምንድነው (WHAT IS MY JOB SONG)**

ይህን ዘፈን ከልጅዎ ጋር ለመዘመር ይሞክሩ እና የማህበረሰብ ረዳት ስራዎችን እንዲገምቱ ያድርጉ። ("ተኝተሃል (Are You Sleeping?") በሚለው ዜማ የተዘፈነውን)

ስራዬ ምንድነው? ስራዬ ምንድነው?መገመት ትችላለህ? መገመት ትችላለህ? ሰዎች እንዲድኑ እረዳለሁ። ሰዎች እንዲድኑ እረዳለሁ። እኔ ማነኝ? እኔ ማነኝ?

ሌሎች ጥቅሶች፤ የውሃ ቱቦዎችን ማስተካከል እችላለሁ። ደብዳቤዎችን አደርሳለሁ። ጣፋጭ ምግቦችን አዘጋጅላችኋለሁ። የቤት እንስሳትዎን ጤናማ እጠብቃለሁ። አዳዲስ ነገሮችን ላስተምርህ እችላለሁ። ከጠፋህ ልረዳህ እችላለሁ።



## ተጨማሪ ሪሶርሶች(RESOURCES)



**ለሥራ የሚሆኑ ልብሶች እና መሳሪያዎችን በሚመለከት ተጨማሪ መጽሐፍት።**

- ሂዝ ሃት ኢዝ ዚስ ? ኤ ሉክ አትሃትስ ዎርከርስ ዌር - ሃርድ፤ ቶል፤ ኤንድ ሻይኒ (Whose Hat is This? A Look at Hats Workers Wear- Hard, Tall, and Shiny) (2005)
- ሁዝ ቱልስ አር ዚስ? ኤ ሉክ አት ቱልስ ዎርከርስ ዩዝ - ቢግ፤ ሻርፕ፤ ኤንድ ስሙዝ (Whose Tools Are These? A Look at Tools Workers Use- Big, Sharp, and Smooth) (2005)
- ሁዝ ሹዝስ? ኤ ሹ ፎር ኤቨሪ ጆብ (Whose Shoes? A Shoe for Every Job) (2011)

©2024 Reading Is Fundamental

Reading Is Fundamental | Read for Success Early Childhood